# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

ተዛማጅ መንጩች:- ABC-RA, BLB, JEA, JEA-RA, JEA-RB, JEA-RC, JEA-RE, JFA-RA, JOA-RA

ኃላፊ ጽ/ቤት:- Chief of Teaching, Learning, and Schools

## የቤት አልባ ተማሪዎች ምዝገባ

I. ዓላማ

ለሌሎች ሕፃናት እና ወጣቶች በተሰጠው መብት መሠረት እያንዳንዱ ቤት አልባ ሕፃን እና ወጣት ተመሳሳይ የመንግሥት ቅድመ ት/ቤት ትምህርትን ጨምሮ አንድ ዓይነት ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት እኩል ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ መስፈርቶችን የሚያወጡ የፌዴራል እና የክልል ሕጎችን ተግባራዊ ለማድረግ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ ቤት አልባ ሕፃናት እና ወጣቶችን የመለየት እና ለትምህርት ቤት የመመዝገብ ሂደቶችን በማቋቋም በተቻለ መጠን የትምህርት አከባቢን ለቀው የመንቀሳቀስ ሁኔታን በመቀነስ የተረጋጋ የትምህርት ስኬት ላይ እንዲያተኩሩ እድሎችን ማመቻቸት። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና ተዛማጅ መመሪያዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች ምዝገባ፣ የትምህርት ክትትል፣ ወይም ስኬት እንደ መሰናክል ሆነውባቸው ሊተገበሩ አይገባም።

ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ተመሳሳይ የስቴት ተማሪ የትምህርት ውጤት መመዘኛዎችን ማሟላት ለማስቻል የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ የማድረግ የፌዴራል ሕግ ድንጋጌ ለማረጋገጥ።

II. ትርጓሜዎች

A. “ትንሽ-ልጅ” እና “ወጣት” ማለት በሜሪላንድ ውስጥ የሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም ትምህርታዊ ፕሮግራም ለመከታተል ብቁ የሆነ ግለሰብን ጨምሮ—

1. ቅድመ መዋእለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል፣

2. ሄድስታርት ወይም ኢቨንስታርት (Head Start or Even Start)፣

3. የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ሕፃናት እና ለትናንሽ ልጆች በ "Child Find" መርሀ ላይ የተሞረኮዘ ልዩ ትምህርት (ስፔሻል ኢጁኬሽን)፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (Early Intervention Program) ጭምር፥ ወይም

4. ሌሎች ፕሮግራሞች (Other programs)

B. “ቤት አልባ ተማሪ” ማለት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ የሚገኘው በጊዜያዊነት ቢሆንም ባይሆንም፣ ቋሚ፣ መደበኛ እና በቂ የሌሊት መኖሪያ የሌለው-የሌላት የቅድመ ት/ቤት ዕድሜ ያለው-ያላት ልጅን

ጨምሮ ትንሽ ልጅ ወይም ወጣት ማለት ሲሆን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመማር ብቁ የሆኑ ለማለት ነው። ይህ ቃል የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

1. ህጻናት ልጆች እና ወጣቶች—

    a) በመኖሪያ ቤት እጦት፣ በኢኮኖሚ ችግር ወይም በተመሳሳይ ምክንያት የሌሎች ሰዎችን መኖሪያ ቤት መጋራት፤

    b) ሌላ አማራጭ ወይም በቂ ማረፊያ ስለሌላቸው በሞቴል፣ በሆቴል፣ በተጎታች ፓርክ ወይም በካምፕ መሬት ውስጥ መኖር፤

    c) በአስቸኳይ ሁኔታ ወይም በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ መኖር[1]፣ ወይም

    d) በሆስፒታል ውስጥ የተጣለ(ች)።

2. መሠረታዊ የሌሊት መጠለያ ያላቸው ልጆች እና ወጣቶች—

    a) መኪና፣ መናፈሻ፣ የሕዝብ መዝናኛ ቦታ፣ ወና የተተወ ሕንፃ፣ አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያ፣ ወይም ተመሳሳይ መቼት ለሰው ልጆች እንደ መደበኛ መጠለያ ሆኖ ያልተዘጋጀ ወይም በተለመደው አይነት ለመኖሪያነት ጥቅም ላይ ያልዋለ የሕዝብ ወይም የግል ቦታ፤ ወይም

    b) ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ወይም ሙቀት የመሣሰሉ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ ወይም ወጣት የሚኖሩበት ሁኔታ መሠረታዊ መገልገያ አለመኖሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል ዝቅተኛ ደረጃ ያለው መኖሪያ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር፤ በተባይ ወይም ሻጋታ የተበከለ እና የሥራ ማእድ ቤት ወይም መጸዳጃ ቤት የመሳሰለ መሠረታዊ መገልገያ የሌለው፤ ወይም ለአዋቂዎች፣ ለልጆች ወይም ለአካል ጉዳተኞች አደጋ ሊያስከትል-ሊደቅን የሚችል ስፍራ።

3. ፈልሰው የመጡ የግብርና ሠራተኞች ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በአንዱ የሚኖሩ ልጆች፤ ወይም

4. የወላጅ/የአሳዳጊ ጥበቃ የሌለው-የሌላት ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት፣ ቤት አልባ ተማሪ።

C. "MCPS homeless liaison" ቤት የሌላቸው ሕፃናት ተለይተው እንዲመዘገቡ እና ሁሉንም ተገቢ የትምህርት አገልግሎቶች እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው። ይህ ሰው በ ቤትአልባ ቤተሰቦች እና በትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ በዋና ጽሕፈት ቤት፣ በመጠለያ ሠራተኞች እና በሌሎች የአገልግሎት ሰጪዎች መካከል እንደ ዋና አገናኝ በመሆን ያገለግላል-ታገለግላለች።

D. "ወላጅ" ወይም "አሳዳጊ" ማለት –

1. ቤት የሌለውን-የሌላትን ተማሪ በህጋዊነት የሚንከባከብና ጥበቃ የሚያሳድግ ወላጅ፣ ግለሰብ ወይም ህዝባዊ ድርጅት፤

---

[1]የማደጎ እንክብካቤ ምደባን የሚጠብቅ-የምትጠብቅ ልጅ ወይም ወጣት እንደ ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት አይቆጠርም። በማደጎ እንክብካቤ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፥ በተጨማሪ የቦርድ ፖሊሲ JEA፣ ነዋሪነት፣ ትምህርት እና ምዝገባ ይመልከቱ። የ MCPS ደንብ JEA-RB፣ የተማሪዎች ምዝገባ ደንብ JEA-RE፣ በትምህርት ላይ የተመሠረተ ምዝገባ እና ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪኮርዶች/መዛግብት።

2. በፍርድ ቤት ትእዛዝ/ውሳኔ የሕፃን ወይም የወጣት ሞግዚትነት የተፈቀደለ(ላ)ት ሰው ወይም ህዝባዊ ድርጅት፤ ወይም

3. ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ወይም 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ወጣት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ የሌለለው-የሌላት።

E. "የመጀመርያው ትምህርት ቤት" ማለት ተማሪው(ዋ) በቋሚነት ሲኖር የተማረ(ች)በት ትምህርት ቤት ወይም ቅድመ ትምህርት ቤት ወይም ተማሪው(ዋ) በመጨረሻ የተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት ማለት ነው። አንድ ተማሪ መጀመሪያ በተከታተለ(ች)በት ትምህርት ቤት የመጨረሻውን የክፍል ደረጃ ሲያጠናቅቅ-ስታጠናቅቅ የመነሻው ትምህርት ቤት የተመደበለትን ተቀባይ/መጋቢ ትምህርት ቤት ያካትታል።

**III. የቅደም-ተከተል ሥርአቶች**

A. የማጣራት እና የብቁነት ማረጋገጫ ውሳኔ

1. ለ MCPS አዲስ ተማሪዎች

a) የአዲሱ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ፣ የ MCPS ቅፅ 560-24 የአዲስ የተማሪ መረጃ፣ የቤት አልባ ምልክቱን ካረጋገጠ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) ቤት አልባ መሆን አለበት ተብሎ ይገመታል።

b) ወላጅ/አሳዳጊ፣ የ MCPS ቅፅ 560-24 ስለ አዲስ ተማሪ መረጃ በመሙላት በደባልነት የሚኖሩበትን ቤት ምልክት ያደረጉ ከሆነ፣ የተማሪው(ዋ) የኑሮ ሁኔታ በቤት አልባ ሁኔታ ውስጥ የተካተተ መሆኑን ለመወሰን ተጨማሪ ማጣራት ያስፈልጋል።

2. በአሁኑ ጊዜ በ MCPS የተመዘገቡ ተማሪዎች

የ MCPS ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ተማሪው(ዋ)ን እንደ ቤት አልባ አድርጎ ካመለከተ(ች)፣ ወይም በመኖሪያ እጦት ምክንያት ተማሪው(ዋ)ን ከት/ቤት ለማስወጣት ከሞከረ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) እንደ ቤት አልባ መቆጠር አለበት።

B. ዋና የሚያስፈልጋትን-የሚያስፈልገውን ነገር ለይቶ ማወቅ

ተማሪው(ዋ) ቤት አልባ እንደሆነ(ች) ከተረጋገጠ፣ የትምህርት ቤት ምደባው አስፈላጊነት ያላቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ውሳኔ ዋና አካል ይደረጋል።

1. መሠረታዊ የፍላጎት ማሟያ አቅርቦት ውሳኔ ስብሰባ ዓላማው ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) መጀመርያ ባለ(ች)በት ትምህርት ቤት መቀጠል ወይም ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ለጊዜው በሚኖርበት-በምትኖርበት አድራሻ ትምህርት ቤት መመዝገብ እንዳለበ(ባ)ት ለመወሰን ነው።

2. በቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ፍላጎት፣ ወይም ከቤት አልባ ወጣት ፍላጎቶች ተቃራኒ ካልሆነ በስተቀር፥ ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) መጀመሪያ ባለ(ች)በት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቀጥል/እንድትቀጥል ማድረጉ የተሻለ እንደሆነ ይታሰባል።

3. ዋና የሚያስፈልጉ ነገሮችን አጣርቶ የመወሰን ስብሰባ የሚከናወነው በ—

a) ተማሪው(ዋ) በወቅቱ በ MCPS ያልተመዘገበ(ች) ከሆነ፤ ወላጅ/አሳዳጊ እንዲመዘገብ/እንድትመዘገብ በሚፈልጉበት ትምህርት ቤት፥ ወይም

b) ተማሪው(ዋ) በአሁኑ ጊዜ የተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት፣ ተማሪው(ዋ) ንቁ የ MCPS ተማሪ ከሆነ(ች)።

4. ዋናውን አስፈላጊ ነገር ተለይቶ የሚወሰንበት ስብሰባ የሚከተሉትን ያጠቃልላል—

a) የወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት ሁኔታን በተመለከተ፥ የ MCPS የቤት አልባ አገናኝ ወይም የ MCPS ቅጽ 335-77 የሞላ(ች) ሞግዚት፣ የቤት አልባ ሁኔታ

b) ርእሰ መምህር/ተወካይ፣

c) የተማሪ ሠራተኛ፣

d) አግባብነት ያለው ትምህርት ቤት እና የዋና ጽ/ቤት ሠራተኞች፥ እና

e) አግባብነት ካለው ቤት አልባ ተማሪ።

5. የተማሪን ዋና ፍላጎት በሚወስኑበት ጊዜ፣ ተማሪ ተኮር-በሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ የእንቅስቃሴ በተማሪው(ዋ) ውጤታማነት እና ስኬት ላይ ተፅእኖ በሚያሳድሩ የትምህርት፣ የጤና እና የደህንነት ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱትን ጨምሮ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል—

a) የተማሪው(ዋ) ዕድሜ፣

b) የተማሪው ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት ትምህርት ቤት፣

c) ተማሪው(ዋ) በነበረ(ች)በት ትምህርት ቤት የነበረው/የነበራት ሁኔታዎች/ተሞክሮዎች፣

d) የተማሪው(ዋ) የትምህርት (አካደሚያዊ) ፍላጎቶች፣

e) የተማሪው(ዋ) ስሜታዊ ፍላጎቶች፣

f) ማንኛውም ሌላ የቤተሰብ ልዩ ፍላጎቶች፣

g) የማስተማር ቀጣይነት፣

h) በወቅቱ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የቆዩበት ያህል ጊዜ፣

i) ወደፊት የቤተሰብ ቋሚ መኖሪያ ሊሆን የሚችል ቦታ፣

j) ከትምህርት ዓመቱ ውስጥ የሚቀረው ጊዜ፣

k) የመጓጓዣ ቦታ ርቀት፣ በተማሪው(ዋ) ትምህርት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፣ እና ሌሎች ተማሪን ማዕከል ያደረጉ የትራንስፖርት ነክ ምክንያቶች፣

l) የተማሪው(ዋ) ደህንነት፣

m) ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤቱ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት/አለማግኘት፣ እና

n) ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤቱ ውስጥ እንግሊዝኛን ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚሰጥ የ (ESOL) አገልግሎቶችን ማግኘት/አለማግኘት።

6. የአካለ ስንኩልነት መኖር በት/ቤት ምደባ መሠረታዊ የፍላጎት ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

a) የእያንዳንዱ ልጅ ምደባ ውሳኔ የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና ስለልጁ-ስለልጅቱ የሚያውቁ የሌሎች ሰዎችን የግምገማ መረጃ ትርጉም እና የምደባ አማራጮችን በማገናዘብ በቡድን መደረግ አለበት።

b) ከቦታ ወደ ቦታ በጣም ተንቀሳቃሽ የሆኑ ቤት አልባ ልጆች ብዙውን ጊዜ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታን ለመከታተል በቂ ጊዜ ስለማይቆዩ፣ በጣም የሚያስፈልጓቸውን መሠረታዊ የፍላጎት ግምገማ ለማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ፥ ቤት አልባ ልጆች ላልታወቀ የአካል ጉዳተኝነት የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

7. ምንም እንኳን በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት ተገቢ ሊሆን ቢችልም ት/ቤት ቤት አልባ ተማሪን ከመደበኛ ትምህርት ቤት አካባቢ ነጥሎ ሊለይ አይችልም።

8. ከወላጆቻቸው/ከአሳዳጊያቸው ተነጥለው የሚኖሩ ቤት አልባ ተማሪዎች ሌሎች ቤት አልባ ተማሪዎች እንደሚደረግላቸው ተመሳሳይ የትምህርት ቤት አማራጮች ይሰጣቸዋል።

9. እንደ መሠረታዊ የፍላጎት ውሳኔ ስብሰባ አካል፣ ወላጅ/አሳዳጊ የ MCPS ቅፅ 335-77 ስለ ቤት አልባ ሁኔታ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመሙላት ያጠናቅቃል-ታጠናቅቃለች። የትምህርት ቤት ምደባን በተመለከተ የመሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮች ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ውሳኔው በ MCPS ቅጽ 335-77 ላይ ሊንጸባረቅ ይገባል። ወላጅ/አሳዳጊ ከትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔ ጋር መስማማታቸውን ወይም አለመስማማታቸውን መግለጽ አለባቸው።

የመሠረታዊ አስፈላጊ ሁኔታ ፍላጎት ውሳኔ ሰጪ ስብሰባ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት በማይስማሙበት ትምህርት ቤት ምደባ ከተደረገ፣ ርእሰመምህር/ተወካይ የ MCPS ቅጽ 335-77A፣ የወላጅ ደብዳቤን በመጠቀም የጽሑፍ ማብራሪያ ይሰጣል። ይህም ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት ውሳኔውን ይግባኝ የማለት ሙብትን በተመለከተ መሰጠት ያለበትን መግለጫ ያጠቃልላል። ሰክሽን I ይመልከቱ።

C. ምዝገባ

1. ለቤት አልባ ተማሪ የተሻለ ጥቅም እንዲሰጥ የተወሰነው ትምህርት ቤት ተማሪው(ዋ) ለመመዝገብ የሚያስፈልጉትን ሠነዶች ለምሳሌ የትምህርት ቤት ሪኮርዶች፣ የልደት የምስክር ወረቀት፣ የክትባት ማስረጃዎች እና የአሳዳጊነት ማስረጃዎች የመሣሰሉትን ተማሪ አሟልቶ ለማቅረብ ባይችልም-ባትችልም እንኳ ት/ቤቱ ተማሪው(ዋ)ን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት።

2. መዝጋቢው ትምህርት ቤት ተዛማጅ ትምህርታዊ እና ሌሎች መረጃዎችን ለማግኘት ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) በመጨረሻ የተማረ(ች)በትን ትምህርት ቤት ወዲያውኑ ያነጋግራል።

3. ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ክትባት ወይም የክትባት/የሕክምና ማስረጃ ማግኘት ከፈለገ(ች) ተቀባዩ (መዝጋቢው) ት/ቤት ወዲያውኑ አስፈላጊውን ክትባት ወይም የክትባት/የሕክምና መረጃዎችን ለማግኘት እንዲያመቻች ወላጅን/አሳዳጊን ወደ MCPS ቤት አልባ አገናኝ (ሊያዘን) ይልካል።

D. ተመጣጣኝ አገልግሎቶች

1. እያንዳንዱ ቤት አልባ ተማሪ በሚማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ለሌሎች ቤት አልባ ተማሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ይሰጠዋል-ይሰጣታል። እንደነዚህ ያሉ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

    a) በትምህርት ቦርድ በተደነገገው የመኖርያ ቦታ ርቀት ክልል ውስጥ ካልተቀመጠ በቀር በዚያ በነበረ(ች)በት ትምህርት ቤት መቀጠሉ የተማሪው(ዋ) ምርጫ/ፍላጎት እንደሆነ ከተረጋገጠ የነበረ(ች)በትን ትምህርት ቤት ጨምሮ የመጓጓዣ አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

    b) ተማሪው(ዋ) ተገቢውን የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟላባቸው-የምታሟላባቸው የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች ለምሳሌ፡- በ Title I የሚሰጡት አገልግሎቶች፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርታዊ ፕሮግራሞች፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስንነት ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ፕሮግራሞችን ጨምሮ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፣ እና በ MCPS የሚተዳደሩ ማናቸውም ሌሎች የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች።

    c) ከትምህርት ሠዓት በፊት እና ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች።

    d) የሙያ እና ዝግጁነት ፕሮግራሞች።

    e) ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሞች።

    f) የትምህርት ቤት ስነ-መጋገብ ፕሮግራሞች።

2. ቤት አልባ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ቤት በሚማሩበት ጊዜ በአጥጋቢ ሁኔታ ላጠናቀቁት ሙሉ ወይም ከፊል የኮርስ ሥራ ተገቢውን ክሬዲት ማግኘታቸውን የሥርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች እና የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ጋር በመመካከር ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ይከታተላሉ። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሂደቶች በፊት በተማሩባቸው የቀድሞው ትምህርት ቤትም በአጥጋቢ ሁኔታ ለተጠናቀቁ ሁሉም ኮርሶች ክሬዲቶችን መስጠትን ያጠቃልላል፣ ትምህርት ቤቱ በሌላ ዲስትሪክት ወይም ከሌላ ስቴት ቢሆን እንኳን፣ በዚያ ትምህርት ቤት ስለ ተማሪው(ዋ) የኮርስ ሥራ ከተማሪው(ዋ) ቀዳሚ ትምህርት ቤት ጋር በመመካከር፣ የተማሪዎችን ወቅታዊ ሁኔታ መገምገም በቅድመ ትምህርት ቤት ውስጥ በከፊል የተጠናቀቁትን ኮርሶች መቆጣጠር፣ ከፊል ክሬዲቶችን መስጠት እና ክሬዲት የሚያገኙባቸውን ኮርሶች መስጠትን ያጠቃልላል።

3. የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቤት አልባ ተማሪዎች ትምህርታዊ እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎችን ተደራሽነት መነፈግ የለባቸውም።

a) የአካዳሚክ ዕድሎች ማግኔት ትምህርት ቤቶችን፣ የሠመር ትምህርት ቤትን፣ የሙያ ዝግጁነት ፕሮግራምን፣ የላቀ ደረጃ ምደባን እና ኦንላይን ትምህርትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

b) የተደራሽነት መሰናክሎች ያመለጣቸውን ማመልከቻ ወይም የምዝገባ ቀነ -ገደቦችን፣ ቅጣቶችን ወይም ክፍያዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ክትባት ወይም ሌላ አስፈላጊ የጤና ማስረጃ፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ ወይም ሌሎች ሰነዶችን ጨምሮ ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሠነዶች፤ ወይም የአካዳሚክ ማስረጃዎች፣ የክሬዲት ማስተላለፊያ ሰነዶችን ይጨምራል።

E. ሪኮርዶች-ማስረጃዎች

ለእያንዳንዱ ቤት አልባ ተማሪ፣ የክትባት ወይም የሕክምና ማስረጃ፣ የአካዳሚክ ሠነዶች፣ የልደት የምስክር ወረቀት፣ የአሳዳጊነት ማስረጃ፣ እና ለልዩ አገልግሎቶች ወይም ፕሮግራሞች ምዘናዎችን ጨምሮ በትምህርት ቤቱ በመደበኛነት የተቀመጠ ማንኛውም ፋይል፣ በ MCPS ደንብ JOA-RA የተማሪ መዛግብት ተማሪው(ዋ) ወደ አዲስ ትምህርት ቤት ወይም አዲስ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በሚገባበት-በምትገባበት ወቅት መገኘት አለበት። ሆኖም፣ የቤት አልባ ተማሪን የኑሮ ሁኔታ የሚመለከት መረጃ እንደ መረጃ አልባ አያስቆጥርም እና በተማሪ መዝገብ ውስጥ እንደ ሌሎች መረጃዎች ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

F. የ MCPS የቤት አልባ አገናኝ (Liaison)

የ MCPS የቤት አልባ አገናኝ ተጠያቂነቱ(ቷ) ለ—

1. ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች በትምህርት ቤት ሰራተኞች ተለይተው እንዲመዘገቡ እና በ MCPS ውስጥ ስኬታማ እና የተሟላ እና እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ፤

2. ነፃ ወይም የዋጋ ቅናሽ ምግቦችን ማዘዝ፤

3. ቤት አልባ ልጆች እና ቤተሰቦች ተገቢውን ጥቆማ ወደ ጤና አጠባበቅ፣ የጥርስ እንክብካቤ፣ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች እና ሌሎች ተገቢ አገልግሎቶችን፣ የአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነትን ማስወገጃ እና መኖሪያን ጨምሮ ማስተባበር፣

4. የትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔዎችን ማፋጠን፣

5. በማህበረሰቡ ውስጥ ቤት አልባ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን እና ቤተሰቦችን ለይቶ ማወቅ፣

6. የአገልግሎቶችን መዛባት/መደራረብ ለመከላከል ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ማስተባበር፣

7. ከሚመለከታቸው የሕግ እና የቁጥጥር መስፈርቶች ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን መከታተል፣

8. ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች የሚኖራቸውን የትምህርት እና ተዛማጅ ዕድሎች ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ማሳወቅ፣ በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ለመሳተፍ ትርጉም ያላቸው ዕድሎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣

9. ትምህርት ቤቶች፣ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች፣ የቤተሰብ መጠለያዎች፣ የሕዝብ ቤተመፃህፍት እና ወጥ ቤቶችን ጨምሮ እንደዚህ ያሉ ልጆች እና ወጣቶች ወላጆች/አሳዳጊዎች በሚገኙባቸው ቦታዎች ቤት አልባ ሕፃናት ወይም ወጣቶች ያሏቸውን የትምህርት መብቶች ይፋዊ ማስታወቂያ ማሰራጨት፣

10. ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት እና ማንኛውም ብቸኛ ወጣት፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወደ የት/ቤቱ መጓጓዣን ጨምሮ ስለ ሁሉም የትራንስፖርት አገልግሎቶች የተሟላ መረጃ ማግኘታቸውን፣ ወደ ተመረጠው ትምህርት ቤት መጓጓዣ እንዲያገኝ-እንድታገኝ እና በምዝገባ አለመስማማት ካለ በዚህ ደንብ መሠረት መፍትሔ መገኘቱን ማረጋገጥ፣

11. በማክኪኒ-ቬንቶ ደንብ (McKinney-Vento Act) መሠረት የ Title I አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስፈልገው ያህል የገንዘብ መጠን የተገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ከ Title I አስተዳዳሪዎች ጋር መሥራት፣

12. ቤት አልባ ሕፃናት እና ወጣቶች ብቁ ሊሆኑባቸው ለሚችሉ ትምህርት እና የተዛማጅ ፕሮግራሞችን የ ESOL አገልግሎቶች፣ ሄድስታርት (ቀድመ-ሄድስታርት ጨምሮ) እና Child Find፣ አገልግሎቶች የመስጠት ሃላፊነት ያለውን የስቴት አስተባባሪ፣ ማህበረሰቡንና የት/ቤት ሰራተኞችን ማስተባበር እና መተባበር፣

13. ቤት አልባ ሕፃናት እና ወጣቶች የትምህርት መብቶች ላይ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን የማሠልጠን መርሃ ግብር ማዘጋጀት እና መተግበር፣ ቤት አልባ ሕፃናትን እና ወጣቶችን ማጣሪያ ማድረግ፣ እና ቤት አልባ ሕፃናት እና ወጣቶች ልዩ ፍላጎቶችን ለማገልገል ፖሊሲዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ እና

14. ከዚህ በታች በሰክሽን G እንደተደነገገው ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቶችን መርዳት።

G. ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቶች

ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቶች በትምህርት ቤት ለመመዝገብ እና ስኬታማ ለመሆን ብዙውን ጊዜ ልዩ መሰናክሎች ያጋጥሟቸዋል። እነዚህ መሰናክሎች ትምህርት ቤት የመከታተል ፖሊሲዎችን፣ የክሬዲት ማጠራቀምን እና ህጋዊ የአሳዳጊነት መስፈርቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ለእነሱ የሚከራከርላቸው እና የወላጅ መብቶችን የሚጠቀሙበት ወላጅ ወይም አሳዳጊ ከሌለ ከምዝገባ ሊከለከሉ እና ረዘም ላለ ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቶችም የትምህርት መብታቸውን ላይረዱ ወይም ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ላያውቁ ይችላሉ። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በወቅቱ ወይም ጨርሶ ላለመመረቅ ተጋላጭ በመሆናቸው ለነዚህ ቤት አልባ ወጣቶች ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

1. ቤት አልባዎችን የሚከታተላቸው ሠራተኛ (liaison) ብቸኛ የሆኑ ቤት አልባ ወጣቶችን በትምህርት ቤት ምርጫ ሂደት፣ ትምህርት ቤት በማስመዝገብ እና ክሬዲታቸው (ውጤታቸው) እንዲተላለፍላቸው በማድረግ ረገድ እገዛ ያደርጋል።

2. የትኞቹ ተማሪዎች በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች አካላዊ ጥበቃ ውስጥ እንደሌሉ ለመለየት የምዝገባ ፎርሞችን በመመርመር የሪጅስትራር ሠራተኞች እና ሌሎች የምዝገባ ሠራተኞች ማገዝ አለባቸው።

3. ቤት አልባዎችን አገናኝ (liaison) እና ሌሎች ሠራተኞች ወላጅ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ በመስጠት፣ የጤና እንክብካቤን እና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ጨምሮ ከሚያስፈልጉዋቸው ሌሎች ድጋፎች ጋር እንዲገናኙ መርዳት አለባቸው። ድጋፍ የሌላቸውና የቤት እጦት ያለባቸው ወጣቶች በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ ስለሚረዳ ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

4. በ IDEA ክፍል B ስር፣ ህዝባዊ ኤጀንሲዎች ብቸኛ ለሆኑ ቤት አልባ ወጣቶች አሳዳጊ ይፈልግ-ትፈልግ እንደሆን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳጊ ወላጅ እስኪሰየምላቸው፣ አግባብነት ያላቸው የአስቸኳይ ጊዜ መጠለያ ሠራተኞች፣ ጊዜያዊ መጠለያዎች፣ በተናጠል የመኖር ፕሮግራሞች፣ እና የመንገድ ማዳረስ ፕሮግራሞችን ሁሉ የሚመለከታቸው የ IDEA መስፈርቶችን የሚያሟላ አሳዳጊ እስኪሰየም ድረስ እንደ ጊዜያዊ አሳዳጊ ሊሰየምላቸው ይቻላል።

5. ቤት አልባ ወጣቶች አንዳንድ ጊዜ የድህረ -ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለማግኘት እና ለማጠናቀቅ መሰናክሎች ሊገጥሟቸው ይችላል። ለምሳሌ:- ለማመልከት የሚያጋጥማቸው ችግር፣ የገንዘብ ዕርዳታ ለማግኘት እና ድጋፍ የሚያገኙበት መረብ አለመኖር።

    a) ቤት አልባ ለሆኑ ወጣቶች ካውንስለሮች ለኮሌጅ እንዲዘጋጁ እና የኮሌጅ ዝግጁነታቸውን እንዲያሻሽሉ ምክር መስጠት አለባቸው።

    b) ቤት አልባ አገናኝ ሠራተኛ (homeless liaison)፣ ከካውንስለሮች እና ከሌሎች ለኮሌጅ ዝግጁነት ከሚሰሩ የ MCPS ሠራተኞች ጋር፣ ሁሉም ቤት አልባ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የኮሌጅ ዝግጁነትን፣ የኮሌጅ ምርጫን፣ የማመልከቻ ሂደቱን፣ የገንዘብ ዕርዳታን፣ እና በካምፓስ ድጋፍ እንደሚያገኙ በእርግጠኝነት መሥራት አለበ(ባ)ት። እንዲሁም በ የ 1965 የከፍተኛ ትምህርት ሕግ አንቀጽ 480 መሠረት፥ በተናጠል ተማሪነታቸው ይህንን ማረጋገጫ ማግኘት መብታቸው ስለሆነ ጉዳያቸው ያለበትን ሁኔታ ለተማሪው/ዋ(ዎቹ) ማሳወቅ አለባቸው።

H. የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች

1. በተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ብዙ ቤተሰቦች ወዲያውኑ ቤታቸውን ሊያጡ ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት አደጋ ወይም በሌላ አሳዛኝ ክስተት ቤት አልባ ለሆኑ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች አገልግሎቶችን ለማመቻቸት ለ MCPS ቤት አልባ አገናኝ (MCPS homeless liaison) ከስቴት አስተባባሪዎች ጋር አብሮ መስራት ወሳኝ ይሆናል።

2. አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ አገናኝ ሠራተኛው(ዋ) "the liaison" ብዙ የተፈናቀሉ ተማሪዎች እንዲመዘግቡ ት/ቤቶችን በማዘጋጀት እና እንደ አስፈላጊነቱ የመለየት እና የመመዝገቢያ ሂደትን የሚያግዙ ተጨማሪ ሠራተኞችን በማዘጋጀት በንቃት መሥራት አለበ(ባ)ት።

3. አገናኙ (The liaison) ቤት ስለሌላቸው ተማሪዎች መብትና አገልግሎቶችን በቀጥታ ለተጎዱት ቤተሰቦች እና ቤተሰቦችን ለሚረዱ ሰዎች ማሳወቅ አለበ(ባ)ት፥ ይህም በ McKinney-Vento የመብቶች ድንጋጌ መሠረት የተፈናቀሉ ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ላይ ፖስተሮችን ወይም ብሮሹሮችን በሚታዩበት ቦታ መለጠፍ እና ማሰራጨትን ሊያካትት ይችላል።

I. በምዝገባ ወቅት የሚነሱ ክርክሮች

1. በትምህርት ቤት ምርጫ ወይም በትምህርት ቤት መመዝገብ ላይ ክርክር ከተነሳ:-

a) ቤት -አልባ ተማሪው(ዋ)ን ወዲያውኑ ተቀብሎ ለምዝገባ ወደሚፈለግበት ት/ቤት ወይም (ወደ መጀመሪያው ት/ቤት ወይም ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ለጊዜው በሚኖርበት-በምትኖርበት አድራሻ ወደሚገኘው ትምህርት ቤት) አለመግባባቱን እስኪፈታ ድረስ የመጓጓዣ አገልግሎት መሰጠት አለበት።

b) ውሳኔውን ይግባኝ የማለት መብትን እና የትርጉም አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ የትምህርት ቤት ምርጫን ወይም ምዝገባን በተመለከተ ትምህርት ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ለወላጅ/ለአሳዳጊ በጽሑፍ ማብራሪያ መሰጠት አለበት። በማብራሪያው ላይ ትምህርት ቤቱ እንዴት ወደ ውሳኔው እንደደረሰ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

1) በት/ቤቱ የቀረበው ወይም ውድቅ የተደረገ የድርጊት መግለጫ።

2) ድርጊቱ ለምን እንደታቀደ ወይም እንደተከለከለ ማብራሪያ።

3) ትምህርት ቤቱ ያገናዘባቸው ሌሎች አማራጮች ዝርዝር መግለጫ።

4) ማንኛውም ሌሎች አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸው ምክንያቶች።

5) ከትምህርት ቤቱ ውሳኔ ጋር የሚዛመዱ ማናቸውም ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ እና ከተገቢነት ወይም ከሁሉ የተሻለ የፍላጎት ውሳኔ ጋር የተዛመዱ መረጃዎች፣ እውነታዎች፣ ምስክሮች፣ እና የታመኑ መረጃዎችን እና ምንጮቻቸውን ጨምሮ።

6) ማንኛውም ተዛማጅ የግዜ ገደቦች እንዳያመልጡ ለማረጋገጥ የሚረዱ የጊዜ ማእቀፎች።

7) የ MCPS ቤት አልባ አገናኝ (MCPS homeless liaison) እና የስቴት አስተባባሪ የግንኙነት መረጃ፣ እና ስለ ሚናዎቻቸው አጭር መግለጫ።

c) ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቶችን በተመለከተ፣ የግጭቱን መፍትሄ እስከሚገኝ ድረስ፥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቤት አልባ አገናኝ "MCPS homeless liaison" ተማሪው(ዋ) የጀመረ(ች)በት ት/ቤት ወይም ቤት አልባ ተማሪው(ዋ) ለጊዜው በሚኖርበት-በምትኖርበት አድራሻ ት/ቤት ወዲያውኑ ተመዝግቦ(ባ) መጓጓዣ መመቻቸቱን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

2. ምዝገባን፣ የትምህርት ቤት ምርጫን እና የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶች በሚከተለው መልኩ ይስተካከላሉ፦

a) ከቤት አልባ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ወላጅ አልባ ቤት የለሽ ወጣት የጽሑፍ ቅሬታ እንደደረሰ፣ ርዕሰ መምህር ቅሬታውን በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ ይፈታል-ትፈታለች።

b) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባው ወጣት በውሳኔው ካልተደሰቱ፣ ወይም ርዕሰ መምህሩ በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ(ች)፣ ወላጁ/አሳዳጊው ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣቱ(ቷ) ለት/ቤቶች ለሱፐርኢንተንደንት በጽሑፍ ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

c) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

d) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ 10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ(ች)፣ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት በውሳኔው ካልተደሰቱ ወላጁ/አሳዳጊው ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት የውሳኔውን ይግባኝ በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርድ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል-ትችላለች በትምህርት አንቀፅ፣ §4-205 (c)፣ የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ እና የቦርድ ፖሊሲ BLB፣ የይግባኝ እና የችሎት አሠራር ሕጎች መሠረት

e) ይግባኙ በደረሰው በ 45 ቀናት ውስጥ ቦርዱ አቤቱታውን በተፋጠነ ሁኔታ ይወስናል።

f) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቸኛ ቤት አልባ ወጣት በቦርዱ ውሳኔ ካልተደሰቱ፣ በ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለሜሪላንድ ስቴት ቦርድ በጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፥ COMAR 13A.01.05.02።

3. ማንኛውንም ይግባኝ ጨምሮ፥ የክርክር አፈታት ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተማሪው(ዋ) በ MCPS ተመዝግቦ ይቆያል-ተመዝግባ ትቆያለች እና በ MCPS መጓጓዣ ይሰጠዋል-ይሰጣታል።

4. በሰክሽን III.A (section III.A) አሠራር መሠረት አንድ ተማሪ ቤት አልባ ነው-ናት ተብሎ ሲገመት ቆይቶ፣ ማስረጃው ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ ከላይ የተገለጹትን ሂደቶች በመከተል በቤት አልባነት የተፈረጀ(ች)በት ሁኔታ ሊቀለበስ ይችላል።

J. ቤት አልባ ተማሪዎችን መለየት እና መመዝገብን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ሰነዶች እና ቅጾች ይመልከቱ:-

1. የ MCPS ቅጽ 560-24፣ የአዲስ ተማሪ መረጃ

2. የ MCPS ቅጽ 335-77፣ የቤት አልባ ሁኔታ

3. የ MCPS ቅጽ 335-77A፣ የቤት አልባ ተማሪ ትምህርት ቤት ምርጫ ውሳኔ

4. የ MCPS ቅፅ 335-77B፣ ለቤት አልባ ተማሪ የትራንስፖርት አቅርቦት ጥያቄ (HSTAR)

5. የ MCPS ቅጽ 560-20፣ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ከትምህርት ቤት መልቀቅ/ህጋዊ የማጣሪያ ፈቃድ (Withdrawal/Clearance)

6. የ MCPS ቅፅ 560-21፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ከትምህርት ቤት መልቀቅ/ህጋዊ የማጣሪያ ፈቃድ (Withdrawal/Clearance)

7. ቤት አልባ ተማሪዎችን ስለመለየት እና መመዝገብ ትምህርት ቤት-ተኮር መመሪያዎች

ተዛማጅ ምንጮች:- Stewart B. McKinney-Vento Homeless Assistance Act, Subtitle B, amended by the No Child Left Behind Act of 2001 (P.L. 107-110), Title X,

Part C, Subtitle B, Education for Homeless Children and Youth; Title I, Part A of the Elementary and Secondary Education Act of 1965, as amended through P.L. 114-95, enacted December 10, 2015; Annotated Code of Maryland, Education Article, §4-205(c); Code of Maryland Regulations §§13A.02.06, 13A.05.02.04, 13A.05.02.13, and 13A.05.09

ስለ ደንቡ ታሪክ፡- አዲስ ደንብ የፀደቀው ኦገስት 28 ቀን 2002 ዓ.ም፥ የተሻሻለው ሴፐተምበር 16 ቀን 2003 ዓ.ም፥ ሜይ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ተገምግሟል፥ ጁላይ 8 ቀን 2021 ተሻሽሏል።